★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 46 ቁ. 2** **ታኅሣሥ/ጥር 2020**

## ወጣቱ ዛሬም ለሀገሩና ለወገኑ ቤዛ ነው!

ኢትዮጵያ ሀገራችን ረዥም ታሪክ ፣ የራሷ ፊደል ፣ የራሷ/ የዘመን አቆጣጠር፣ የራሷ ፍልስፍናና የሥነጽሁፍ ዘይቤ (ቅኔ)፣ ከሌሎች ለየት ያሉ የበዓላት አከባበር፣ ልዩ (ያሬዲያዊ) ዜማ ፣ ጥበብና ኪነጥበብ ባለቤት ከመሆኗም በተጨማሪ ብዙ ጀግኖች ያፈራች ሀገር ነች፡፡ እነዚህን ታላቅ ፀጋዎች መሠረት አድርጋ በዕድገት ጎዳና ወደፊት መራመድ እንዳትችል የውጪና የውስጥ ፈተናዎች በዚያው ልክ እንቅፋት ሆነው ሲፈራረቁባት እንደቆዩ ቀደም ያለው ታሪኳ ይመሠክራል፡፡ የቅርቡን ስናይ ደግሞ ኢትዮጵያ ከአምባገነን አገዛዝ አዙሪት መውጣት ባለመቻሏ ግፍና በደል ትውልድ ተሻጋሪ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይባስ ብሎ፣ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ከወራሪ ጠላት ባልተናነሰ ከውስጥ በፈሉባት ዘረኞች እጅ የወደቀችበት፣ ሕዝቧ የዜግነት መብቱን የተነፈገበት፣ ሰብዓዊ መብቱ (የተፈጥሮ መብቱ) የተረገጠበት፣ ተነግሮ የማያልቅ ግፍና ሰቆቃ የሚቀበልበት፣ ዳር ድንበሯ የተደፈረበት፣ ባህር በሯ የተዘጋበት፣ ብሔራቸው ከገዥው ፓርቲ ብሔር ውጭ ያሉ ዜጎች በተለይም አማራውና ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ ታይቶ በማይታወቅ አረመኔነት ፍጅት የተካሄደ ከመሆኑም በላይ በሥልጣን የተቀመጡ ጥቂት ቅምጥሎች አንጡራ ሀብቷን ተቀራምተው የዛሬውን ብቻ ሳይሆን መጭውንም ትውልድ ዕዳ ወራሽ ሲያደርጉት እናያለን፡፡ ይባስ ብለው ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንዳትቀጥል፣ ቋንቋን መሠረት ባደረገ የብሔር ፌዴራሊዝም ሸንሽነው ሀገራዊ ህልውናዋን ተጋፍተው ጠርዝ ላይ አድርሰዋታል፡፡ በዚህ ተከታታይ የሀገር ክህደት ወንጀል ግንባር ቀደም ሰለባ የሚሆነው ደግሞ ብዛቱ ከሀገሪቱ ሕዝብ 70 እጅ በላይ የሆነው ወጣት በመሆኑ ተስፋና ጨለማ ያዘለ መጻኢ ጊዜ እንደሚጠብቀው መገንዘብ እንገደዳለን፡፡ ወጣቱ በሀገሩ የመኖር መብትም ሆነ የሥራ ዕድል ተነፍጎት፣ መንገድ ላይ አዳሪ፣ የአደንዛዥ ዕፅና የዘቀጠ ባህል ሰለባ ከመሆኑም በላይ በስደት የበረሃና የዓሳ ነባሪ ቀለብ በመሆን፣ በዓረቡ ዓለም ለከፋ ዘረኝነትና ባርነት በመጋለጥና በዚያ በሚገኙ ዕስር ቤቶች በገፍ በመታጎር፣ በድብደባ፣ በረሃብና በእርዛት እየተሰቃየ ይገኛል። ኢትዮጵያ ከራሷ የወጣ ጠላት እንጅ የራሷ መንግሥት የላትም የምንለው እንዲሁ በከንቱ አለመሆኑን፣ በሙቶ ሽህዎቹ የሚቆጠሩ ተፈናቅለው በየሜዳው የወደቁ ዜጎቿና፣ ተሰደው በባዕዳን እጅ እየተሰቃዩ ያሉት ወጣቶች ይበልጥ ይረዱታል፡፡

ከዚህ ሁሉ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ባለው መከራ የባሰ የሚሆነው ደግሞ ለዚህ ሞልቶ ለፈሰሰው ለወገን ግፍና ሰቆቃ ጎልቶ የሚታይ ቁጭት አለ ብሎ ለመናገር ማስቸገሩ ነው፡፡ ሀገርን በነፃነቷ የምንኮራባትን ያህል በመከራዋ የምንሸሻት ባለመሆኑ፣ እያንዳንዱ ትውልድ በጊዜው ለገጠሙት ሀገራዊ ጥያቄዎች በሚቻለው ሁሉ ምላሽ ሊሰጥ፣ የራሱን ታሪክ ሊሰራ፣ የትግል ተመክሮውን ለቀጣዩ ሊያስተላልፍና አሻራውን ሊተው ይጠበቃል፡፡ የኃያሉን የጣሊያን ፋሽስት ወራሪ፣ ዘመናዊ የጦር መሳሪያና የመርዝ ጪስ ተቋቁሞ ነፃነትን ከመቀዳጀት በላይ የከበደ የትውልድ ፈተና የለም፡፡ ሆኖም ይህ ከኛ አቅም በላይ ነው ሳይል ለነፃነቱ ታግሎ አሸነፈ አንጅ "ሲ ማይስትሮ" - እሺ ጌታዬ - ብሎ አልተንበረከከም፡፡ የ1960-ዎቹ፣

ህይወቴን ለሀገሬና ለሕዝቤ ያለው ትውልድም ይህንኑ የጀግንነት ቅርስ ነበር የወረሰው፡፡ የአንድ ሀገር ቀጣይነት፤ ልማትና ዕድገት የሚለካው ሀገሪቱ ባላት ሀብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን መልካም እሴቶቿን ተረክቦ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ የሚችል፤ ለቀጣይ የሀገሪቷ የዕድገት ጎዳና ራዕይ ኖሮት ወደላቀ ደረጃ እንድትደርስ የሚሠራ ለዚያም በጽናት የሚቆም ትውልድ ሲኖራት ነው። ይህ በመሆኑ ነበር፣ ያ ትውልድ እስከ አንገቱ የታጠቀውን ወታደራዊ አገዛዝ ያለቦታው ገብቶ ረግጨ ልግዛችሁ ሲልና ለሕዝቧ የተበላሸ ራዕይ ሲያስቀምጥ የለም ያለው። ለአገሪቱ የወደፊት ዕድገትና የዴሞክራሲያዊ ትውልዱ ያለው ራዕይ ጠንካራና ዘላቂ ስለነበር ነው በቆራጥነትና በሕዝባዊ ወኔና ክብር ፋሽስቱን ደርግ ብርክ ያስያዘውና በምትኩ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ይመጣ ዘንድ ይታገል የነበረው። ለዚህም ነው ሀገር በታኝ ጠባቦች ሥልጣን ከመያዛቸውም በፊት ሆነ ሥልጣን ከያዙ በኋላ ሀገር መበተን የኢትዮጵያውያን ታሪክና እሴት አይደለም፤ ሀገራችን ሉዓላዊነቷና አንድነቷ አይነካም፣ አትበተንም የሚል አቋሙን አጽንቶ ካባቶቹ በወረሰው ወኔ የተጋፈጣቸውና የታገላቸው፣ አሁንም የሚታገላቸው።

ወጣት ትውልድ ባጠቃላይ ሲታይ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል የወጣ እንደመሆኑ ሁሉ የኅብረተሰቡ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሥነልቡናዊ ትስስርና የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ነፀብራቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት ገበታ ግንኙነቱ፣ ነገሮችን ለማወቅ፣ ለመጠየቅና ለመመርመር አጋጣሚው ይፈቅድለታል፡፡ በዚህም ከአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የተሻለ አጋጣሚ ላይ መገኘቱ፣ ትኩስ ኃይል እንደመሆኑ፣ አዲስ ራዕይ፣ አዲስ ተስፋ፣ አዳዲስ ነገር ናፋቂና ለውጥን የሚሻም ነው፡፡ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዬውን በደልና የፍትሕ መዛባት አስቀድሞ ስለሚረዳ፣ በሕዝብ በደል ይቆጫል፤ ለትግልም ይነሳሳል። ኅበረተሰቡ የነገውን የተሻለ የለውጥ ጎዳና ያይ ዘንድ ቀድሞ በመሰለፍ፣ የትግልን ገፈት ቀማሽ ለመሆን ቁርጠኝነቱ ስላለውም፣ ሀገርና ወገን ከወጣቱ ብዙ ይጠብቃል። ኢትዮጵያ ለዜጎቿ ብቻ ሳይሆን ለነጻነታቸው የሚዋጉ የዓለም ሕዝቦች አርዓያ የሆነው የትናንት አርበኛና ለወገኖቹ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር አንገቱን የሰጠው ቀጣይ ትውልድ ሀገር ነች፡፡ የ60ዎቹ ትውልድ የታገለለት ሕዝባዊ መንግሥት በፋሽስታዊ አገዛዝ ቢጨናገፍም፣ ያነሳቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች ዛሬም መልስ ያላገኙ ወቅታዊ መፈክሮች ናቸው፡፡ የትግሉ አልፋና ኦሜጋ የሆነው የማኅበራዊ ፍትህና የዕኩልነት ጥያቄና የህ ዕውን እንዲሆን በተደረገው ትግል ከተካበተው ተመክሮ ቀጣዩ ትውልድ ይማርበት ዘንድ ታላቅ ቅርሱን ትቶለት አልፏል፡፡ የወታደራዊ ጁንታው ካድሬዎች፣ ወያኔም ሆነ፣ እሱን የተኩት የጡት ልጆቹ፣ ይህንን ታሪካዊ ሀዲድ ለመስበር፣ ያልፈጠሩት የውሸት ትርክት ባይኖርም፣ በደም የተፃፈ ታሪክ ነውና በምንም አይነት ጫጫታ የሚዋጥ አይሆንም፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በረዥም ዘመን ታሪኳ ከመለስተኛ እስከ ህልውናን ተፈታታኝ ችግሮች ገጥመዋታል፡፡ የማንንቷ መገለጫ የሆኑት ቆራጥ ዜጎቿም በሀገር ልዕልናና በነፃነታቸው ላይ የመጣ ማንኛውንም ጥቃት ወይም የውስጥ ችግር እንደዬ አመጣጡ ተጋፍጠው ነጻነትና ክብሯን ጠብቀው አስቀጠሏት እንጅ፣ ባርነት ትውልድ ተሻግሮ ለልጆቹና የልጅልጆቹ እንዲተርፍ አልፈቀዱም፡፡ ጊዜ ያመጣውን ጊዜ አስኪመልሰው በሚል የቁም ሞትን አልመረጡም፡፡ በተመሳሳይ ከንቱ ሽንፈትም የታሪክን አደራ አልበሉም፡፡ በዚህ አኩሪ ታሪኳም ቀደም ሲል ተነስተው የነበሩ ኃያላን አክብሮታቸውን ባይነፍጓትም፣ ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ አፍሪካን እንደ ቅርጫ ተከፋፍለው በቅኝ ግዛት የተቀራመቱ ኃያላን ሀገራት ኢትዮጵያን በቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ስር ማስገባት የሚቻል አለመሆኑን ሲረዱ፣ ጥርስ ነክሰውባት በዙሪያዋ ተንኮል ሲያጠነጥኑ ቆይተዋል፡፡ የውስጥ ጠላት የብብት እሳት እንዲሉ፣ የሰውን ልጅ ድክመት በመሣሪያ መግደል አይቻልምና፣ ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባት፣ ሙስሊምና ክርስቲያኑ እንደየእምነታቸው ተከባብረው፣ ተባብረውና ተዋልደው ለዘመናት በሰላም

የሚኖሩባትን ብቸኛ አገር ከፋፍሎ ለማዳከም፣ የራሷን ከሀዲ ባንዳዎች በገንዘብ ኃይል አደራጅተው፣ የሌለ ማንነትና ታሪክ አሳቅፈው፣ በሰሜንና ደቡብ ተገንጣይ ኃይላትን በነፃ አውጭ ሽፋን አስነሱባት፡፡ የአፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በታች ያሉት ሀገሮች የተፈጥሮ ሀብት የምዕራባዊያን ብልጽግና መሠረት በመሆኑ፣ የአካባቢው አገራት የሀብታቸው ተጠቃሚ የሆኑለት ብልፅግናቸው የሚያበቃለት መሆኑን እነሱም ሊያስተባብሉት የማይችሉት ሐቅ ነው፡፡ በመሆኑም በተለመደው የቅኝ ገዥዎች ከፋፍለህ ግዛ ታክቲክ ጎሳን ከጎሳ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨትና ከቅኝ ገዥው የባሱ አረመኔ አምባገነኖችን ወደ ሥልጣን በማምጣት፣ የተማረውን ኃይል (አምራቹን ትውልድ) በማሸማቀቅ የራሱን ሳይሆን የሰው ሀገር እንዲያለማ ወደ ስደት ገፍተው የዕድገት በርን ከመዝጋታቸው ሌላ፣ አንጡራ ሀብቱን ዘርፈው የባዕዳንን ባንኮች ያደልባሉ፡፡ መተባበር የሚገባቸውን ጎረቤት ሀገራት እርስበርስ በማጋጨትና በመሳሰለው ውጥረት ተዳክመው ከብድርና/የድህነት አዙሪት እንዳይወጡ ያደርጓቸዋል፡፡ ይህንኑ አስከፊ አገዛዝ የሚደጉሙት ባዕዳን መልሰው ያንኑ የተበደለ ሕዝብ ራሱን መምራት እንደማይችል አድርገው ይሳለቁበታል፡፡ ይህን መሠሉን የቅኝ ገዥዎች የማራኮት ስልት ነው፣ የኛዎቹ ሚሽነሪ ሰራሽ፣ ነፃ አውጭዎች አንዴ ምኒሊክን ሌላ ጊዜ አማራውን ጠላት አድርገው የቆሙት፡፡ ስለዚህ ሀገራችን ዛሬ የደረሰችበትን ውስብስብ ሁኔታ በቅጡ ለመረዳትና መውጫ መንገድን ለመቀየስ፣ ለዚህ ያበቃትን መነሻ ምክንያት መቃኘት ተገቢ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡

ከሁለተኛው የጣሊያን ወራሪ ሽንፈት ማግስት፣ ንጉሡ ከ5 ዓመት የእንግሊዝ አገር ቆይታቸው በኋላ አገር ገብተው ወደ ንግሥናቸው ሲመለሱ፣ መዲናዋ ላይ በስማቸው አንድ አውራ መንገድ የሰየሙላቸው የወቅቱ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቴር ፣ በጣሊያን ጦር መሪዎች ጦር ላይ የጦር ወንጀል ክስ እንዳይከፍቱ አድርገው ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ወዳጅነት ከማይታሙት ምዕራባዊያን መሪዎች አንዱ ነበሩና፣ ንጉሡ ለሥልጣናቸው ዋስትና ሲሉ በሚስጥር የገቡባቸው ሌሎች ተመሳሳይ ውሎች ሊኖሩ እንደሚችሉና እንደምታቸው ለሀገር እንደማይበጅ በወቅቱ የጠረጠሩትን አርበኞች ባገለለ፣ ለጣሊያን ያደሩትን ባካተተ፣ ንጉሡ ስልጣናቸውን አደላደሉ፡፡ ኢትዮጵያም ከደብረ ታቦር ጀምሮ አስከ ደቡብና ምዕራብ ግዛቷ በሃይማኖት ሽፋን ለሚሰልሉ፣ የክፍፍል ችግኝ ለሚተክሉ የፕሮቴስታንት፣ ካቶሊክ ሚሲዮናዊያንና ምልምል ፒስ ኮሮች በሯ ክፍቱን ተለቀቀ፡፡

የባዕዳንን ቋንቋ፣ ወግ፣ ዕምነትና ታሪክ አጉልቶ፣ የኢትዮጵያ የሆነውን የሚያደበዝዝ የትምህርት ሥርዓትም አብሮ ተዘረጋ፡፡ ይህን የትምህርት ሥርዓት እንዳለ ተቀብለን በሥራ ካዋልነው ለሀገሪቱ አደጋ እንደሚኖረው ቀድመው ያስጠነቀቁት የመጀመሪያው የትምህርት ሚኒስቴርም ወዲያውኑ ተነስተው በሌላ አገልጋይ እንዲተኩ ሆነ፡፡ የዜጎቿ ሀገር ወዳድነት፣ በማንነታቸው ኩራትና ለነፃነታቸው አይበገሬነት ቀስበቀስ እየተሸረሸረ ሄዶ፣ የራሳችን የሆነው በቅጡ ሳይታወቅ፣ የባዕዳንን ታሪክ ማነብነብና የነሱን ቋንቋ አቀላጥፎ መናገር የዕውቀት መለኪያ ሆኖ መታየት ጀመረ፡፡

ይህ በሚሆንበት ወቅት፣ ብዙ የአፍሪካ አገራት በቅኝ አገዛዝ ስር እየማቀቁ የነበሩበት፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በሞዛምቢክና በኢያን ስሚዟ ዚምባቡዌ ዘረኛ አገዛዝ ብዙ ግፍ የሚፈጸምበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በቅኝ አገዛዝ ሲማቅቁ የነበሩት የአፍሪካ አገራት፣ እንደነ ኮንጎ፣ ናይጀሪያ፣ ሶማሊያ፣ ሴኔጋል፣ ሱዳን፣ ቻድ፣ አይቮሪ ኮስት፣ ካሜሩን፣ ጋቦን፣ ማዕከላዊ አፍሪካና ሌሎችም ነፃነታቸውን ከብሪታኒያና ፈረንሳይ በመላቀቅ ተቀዳጅተው ነበር፡፡ የፀረ-ቅኝ ግዛትና አብዮታዊ እንቅስቃሴ በዓለም ላይ እየተበራታ የመጣበት፣ ቀደም ሲል በሶቪየት፣ ቀጥሎም በቻይና የተካሄደው አብዮት የትግል መነሳሳትን የፈጠረበት ሁኔታ ነበር፡፡ የኩባዊ ባቲስታ ተወግዶ በነካስትሮ ድል መጠናቀቁ፣ የወጣቱን ቀልብ የሳበው የቸጉቬራ ዓለም ዓቀፋዊ

አርበኝነት፣ ካምቦዲያዊያን ሀገራቸውን ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ቀጥሎም ቬትናማውያን እንዲሁ ከሰሜን ቬትናም (ከኢንዶ ቻይና) ፈረንሳይን ያስወጡበትና በአልጀርያ ፀረ ቅኝ አገዛዙ ትግል የተጠናከረበት ወቅት ነበር፡፡ ስለዚህ በዓለም ዙሪያና በአካባቢው አገሮች ይካሄዱ የነበሩ የነፃነት እንቅስቃሴዎችና አብዮታዊ ለውጦች፣ ተወደደም ተጠላ እንደሌሎቹ አገሮች፣ ኢትዮጵያም ውስጥ በነበሩ እንቅስቃሴዎችና የለውጥ ጥያቄዎች ላይ የማይናቅ ተፅዕኖ ነበራቸው፡፡ ሀገራችንም ከዚህ ሁለንተናዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ውጭ ሆና የምትታይ ልዩ ደሴት አልነበረችም፤ ወይም ደግሞ በግራ ሳይሆን ለምን የቀኙን መስመር አልያዘችም ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት አይቻልም። አንድ ትውልድ በዘመኑ የወደፊት ተስፋና የለውጥ ራዕይ ሊኖረው ይገባል፡፡ በትውልድም ሆነ በታሪክ ፊት የሚያስጠይቀው ነገር ቢኖር፣ ሁሉቱንም ካጣና ምንም ሳይሆን፣ እንዲሁ ምድሪቱን አጣቦ ካለፈ ብቻ ነው፡፡

<u>በሀገራችን ትውልድ ቴዎድሮስን ሳይሆን ቸርችልን፣ የነያሬድን ሳይሆን የነሞዛርትን፣ ዘራ ያዕቆብን ሳይሆን የነስፒኖዛን ወይም ፕሌቶን፣ ላሊበላን ሳይሆን የሮማን ኢምፓየርን የሥልጣኔ መሥፈርቱ አደረገ፡፡</u> ይህ ሲባል የሌሎች በዓለም ላይ ያሉ የፍልስፍና፣ የባህላዊና የሥልጣኔ ቅርሶች እንዲሁም የታዋቂ ግለሰቦችን ታሪክ አንማርባቸው ለማለት አይደለም፤ የሀገራችንን ጥለን እነዚህን ማስቀደም ሲሆን ነው ችግሩ። ዕውቀት የስሌት፣ የሂሳብ፣ ጥቅምን መፍጠሪያ ሆነ፡፡ ዘመናዊነት ከሀገር በቀሉ ይልቅ በውጭ ያኗኗር ዘዬ በመቃኘቱ በሀገሪቱ ማንነት ላይ የተደባለቀ ተፅዕኖ ፈጠረ፡፡ የሀገራችን ቁልቁል ጉዞም በዚያው ልክ ቀጠለ። የዘውዱ አገዛዝም እስካለ ዕድሜውን በማራዘም ገዝቶ ለማለፍ እንጅ መጭው የሀገሪቱ እጣ ምን ሊሆን እንደሚችል ደንታ አልነበረውም፡፡ በወቅቱ የመሬት ጥያቄ መሠረታዊ ቦታ ሊይዝ የቻለው፣ ከ90 እጅ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር የሚኖርና ኢኮኖሚያዊ ተግባሩ ከዚህ ጋር የተያያዘ በመሆኑም ነበር፡፡ እርሻ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እምብርት እንደመሆኑ መጠን በመሬት ይዞታ ላይ የሚደረገው ለውጥ በኢኮኖሚው ዕድገት ላይ አዎንታዊ ውጤት እንደሚያመጣ በጊዜው ብዙ የተባለለት ጉዳይ ነበር፡፡ አጅግ ኋላ ቀር በሆነ የግብርና መሣሪያዎች ታግዞ የሚሠራው ገበሬ ኑሮው ከዕለት ዕለት እየደቀቀ በድብቅ ረሀብተኛ የሆነበትና አስከፊ የባላባት ሥርዓት የሚሰቃይበት፣ ልጆቹ በለጋ ዕድሜያቸው ትምህርት ቤት ሳይሆን ለዕረኝነትና ግብርና ሥራ ይገደዱ ነበር፡፡ ደገኛው ያለመጫሚያ በቁር፣ ቆለኛው በሀሩር የሚሰቃይበት፣ ከሚወለዱት ህፃናት ከሃያ እጁ በላይ አምስት ዓመት ዕድሜ ሳይደርሱ ይሞቱ የነበረበት፣ ሠራተኛው በዘረኛ የባዕድ ኩባንያዎች እጅ መብቱ ተገፎ የሚበዘበዝበት፣ ተመራቂው ያለዘመድ ሥራ የማያገኝበት፣ ፍርድ ቤቱ ድሀውን ሕዝብ በ10ና 15 ዓመት ቀጠሮ የሚያጉላላበት፣ ይባስ ብሎም በሙስና የዘቀጠበት፣ አስከፊ በነበረው የመሬት ሥሪት፣ ጭሰኝነትና የመሬት ግብር ከአቅሙ በላይ የተጫነበት፣ በብልሹ ሹማምንት ግዴለሽነት ደጋግሞ በሚከሰት የረሀብ አደጋ ገጠሬው በገፍ የሚያልቅበት፣ ከረሀብ ሸሽተው ወደ መናገሻ የመጡትን አርሶ አደሮች ከዋና መንገዶች ርቀው የተጣሉበት በአንድ በኩል፤ በንጉሡ ዙሪያ የነበሩ ጥቂት መሣፍንት፣ መኳንንት፣ ቢሮክራትና አቀባባይ ከበርቴው ደግሞ ከሀገርና ሕዝባቸው ተነጥለው ከሌላ ዓለም የመጡ መስሏቸው በሕዝብ ላይ ሲንደላቀቁ፣ አብዛኛው ሕዝብ ደግሞ በገዛ አገሩ ባይተዋር ሆኖ ቡትቶውን ተከናንቦ ተንቆና ተረግጦ ይኖር ነበር፡፡ እነዚህ ጉልህ ሆነው የሚታዩ ሁለት የሀገሪቱ ተቃራኒ ገፅታዎች ነበሩ፡፡ በተጨማሪ፣ ሌሎችንም አስከፊ የነበሩ የወቅቱ ጉዳዮች በቅርብ ላጤነ፣ ሀገሪቱን ቀይቶ የገጠማት ችግር ዱብ ዕዳ እንዳልነበር በቀላሉ ይረዳል፡፡

በመሆኑም፣ በንጉሡ ላይ የነበሩ ምሬቶች እየተባባሱ ሄደው፣ በብቸና፣ በባሌ፣ በጌዲዮ፣ በስሜንና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች የገበሬው አመፅ የተጀመረበት፣ የምድር ባቡርና ወንጅ ስኳር ሠራተኞችም በነአበራ ገሙ መሪነት በማህበር የተደራጁበትና ለተሻለ ክፍያና የሠራተኛ መብት መከበር የሥራ ማቆም አድማ የጀመሩበት፣ ወታደሩ የደሞዝ ጭማሪ

የጠየቀበት፣ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የታቀደውን የራዛ ፕሮጀክት የተቃወመበት፣ የኮሪያ ዘማቾች በብልሹው አስተዳደር በተወሰደባቸው ገንዘብ ተቃውሞውን የተቀላቀሉበት፤ …ወዘተ ውስጥ ለውስጥ ሲብላሉ የነበሩ ብሶቶች ወደ አደባባይ የወጡበት ሁኔታ ነበር፡፡ በአጭሩ የሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እየከፋ መሄዱንና ሕዝብ ለውጥ መፈለጉን ንጉሣዊው አስተዳደር ልክ እንደተራ ጉዳይ ቦታ አልሰጠውም፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ቀደም ሲል የተረዱት ሀገር ወዳድ መኮንኖች፣ በ1953 ዓ.ም ወርሃ ታህሣሥ ላይ ማንም ሊያስብ እንኳን ያልደፈረውን ጉዳይ ነበር ለአደባባይ ያበቁት፡፡ በጊዜው ተራማጅ የነበሩ የክቡር ዘበኛ መኮንኖች፣ በተለይም እንደገርማሜ ንዋይና መንግሥቱ ንዋይ አይነቶች የሀገራቸው ኋላ ቀር መሆን አሳሳቢ እንደሆነ የተረዱ መኮንኖችና አርበኞች፣ ሀገሪቱ ወደፊት እንዳትራመድ ማነቆ የሆነው ባላባታዊ አስተዳደር ተወግዶ፣ በቦታው ሕገ መንግስታዊ ንጉሣዊ አገዛዝ መተካት፣ ማለትም ልክ በጃፓንና እንግሊዝ እንደሚታየው ንጉሡ ርዕሰ ብሔር ሆኖ፣ ሥልጣን ግን በፓርላማው እጅ ለማድረግ ነበር፡፡ በታህሣሥ 1953 ዓ.ም በሁለቱ ወንድማማቾች እና በእነወርቅነህ ገበየሁ፣ ጀኔራል ጽጌ ዲቡ፣ ባዬ ጥላሁን የተመራና ተሳካ የተባለው መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ ጦር ሠራዊቱን ከክቡር ዘበኛው ጋር በማጋጨት አሜሪካኖች ሊያከሽፉት ችለዋል፡፡

እኒህ ሀገር ወዳድ መኮንኖች፣ ተቀማጥለው ከሚኖሩበት ህይወታቸው ሀገራቸውን፣ ወገናቸውን በማስቀደም፣ በአደባባይ ተሰቅለው ውድ ህይወታቸውን መስዋዕት አድርገዋል፡፡ እንደቀደምት ወጣት አርበኞች እንደነአብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም፣ ሀኪም ወርቅነህ እሸቴ፤ ከሴት ወጣት አረበኞች እንደነሸዋረገድ፣ ከበቡሽ፣ ፋንታየ፣ …ወዘተ የኋለኞቹም በጀግንነት ለሀገራቸው ተሰውተዋል። ለመጪው ትውልድ የሀገር ወዳድነትና ጀግንነት አርዓያ ሆነዋል፡፡ የማይደፈር ይመስል የነበረው የንጉሡ ነገሥቱ ኃይል፣ ሊገሠሥ፣ ሊደፈር እንደሚችልም አሳይተዋል፡፡ ላመኑበት ዓላማ፣ ያዋጣል ላሉት ግብ ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ ለንጉሡ ግን ይህ ሁኔታ እንደ ማስጠንቀቂያ አልሆነላቸውም፡፡

የሥርዓቱ አደግዳጊዎች ይህንን ታላቅ የለውጥ አሻራውን ትቶ ያለፈ ታሪካዊ እርምጃ “የታህሣሥ ግርግር" በሚል አጣጥለው ታሪክን ሊያድበሰብሱ ሞክረዋል፡፡ ዛሬም ይህንኑ ብረዛ የሚያስተጋቡ አሉና በዚህ አጋጣሚ ይብቃችሁ፣ ይቁም ሊባሉ ይገባል፡፡ በዚህም ተባለ በዚያ፣ የተጀመረው እንቅስቃሴ ከላይ የተዳፈነ ቢመስልም ውስጥ ውስጡን ስር እየሰደደ ነበርና ብዙም ሳይቆይ ወጣቱ ትውልድ የትግል አርማውን አነሳ፣ በ1957 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የመሬት ላራሹን ጥያቄ ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ፡፡ በ1959 የተማሪዎች ማኅበር እየተጠናከረ በመምጣቱና በየጊዜው ሰላማዊ ሰልፍ በመካሄዱና ፀረ-ኢምፐሪያሊስት፣ ፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ዘረኝነት ዓለም አቀፋዊ አቋም እየያዘ በመምጣቱ የተደናገጠው የአፄ ኃይለስላሴ መንግሥት፣ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በቅድሚያ መንግሥትን ስለማስፈቀድና አደገኛ የመሰሉትን ተማሪዎችም ለሶስት ወር አግቶ የሚያስር ለመሆኑ ሕግ አወጣ፡፡ ነገር ግን ይህን እገዳ በመቃወም ተማሪው ሰላማዊ ሰልፍ ወጣ እንጅ፣ መንግሥትን ለመቃወም፣ የመንግሥትን ፈቃድ መጠበቅን ለመሰለው መጃጃል ቦታ አልነበረውም፡፡ ብዙዎች ቢታሰሩም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የትግል አጋርነታቸውን ስላሳዩ የታሰሩት በሙሉ ተፈቱ፡፡ በ1962 የተማሪው ማህበር ቀስበቀስ ሥርዓቱን ወደ መጠየቅና ወደ ትግል የተሸጋገረበት ዘመን ሆነ፡፡ በነመንግሥቱ ንዋይ የተከፈለው የመስዋዕትነት ፅዋ በነጥላሁን ግዛው ተደገመ፡፡ በ1962 ዓ.ም "ጥላሁን ለምን፣ ለምን ሞተ?" በሚል ያስተጋባው የተማሪዎች ጥያቄም የትግል ችቦ ሆኖ አበራ፡፡ ተደራጅቶ የመታገልን አስፈላጊነት አበክሮ አስተማረ፡፡ ታሪካዊው የነመንግሥቱ ንዋይ አንቅስቃሴም በቀጣይ ብሩህና ሞት አይፈሬው የነጥላሁን ግዛው ወጣት ትውልድ ተተካ፡፡

ፊውዳላዊው ሥርዓት እጅግ ኋላ ቀርና መለወጥ እንዳለበትም በተራማጅ ምሁራን መካከል ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ መተማመን ነበር፡፡ በ50-ዎቹና በ60-ዎቹ ዓመታት "መሬት ላራሹ" በሚል አብይ መፈክር በወቅቱ የትምህርት ዕድል ያገኙትና አይናቸውን የከፈቱት ተራማጅ ምሁራን፣ የአርሶ አደሩ በደል ስለተሰማቸው፣ ስቃዩ ስለቆጠቆጣቸው፣ ችግሩ ስላመማቸው ስር ነቀል የመሬት ይዞታ ለውጥ እንዲደረግ፣ መሬት ለአርሶ አደሩ እንዲሆን “መሬት ለአራሹ” በሚል መፈክር ብርቱ ትግል አካሂደዋል፡፡ በዚህም ብዙዎች ታሰረዋል፣ ተግዘዋል፣ ተገድለዋል፡፡ ብዙ መስዋዕትነትንም ከፍለዋል፡፡ እንዲሁም ሠራተኛው፣ ተማሪና አስተማሪው፣ አርበኛው፣ ወታደሩ፣ ታክሲ ነጅው፣ ሳይቀር በአንድም ሆነ በሌላ መልክ የዘውዱ ሥርዓት ላይ የነበረውን ተቃውሞ ይዞ የተነሳበትና ለለውጥ ያለውን ፍላጎት ያሳየበት ወቅት ነበር፡፡ ወጣቱ ምሁር ከሀገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግሉን ያስተባበረበት፣ የመሬት ላራሹ ጥያቄ አብይ ጥያቄ አርጎ የወጣበት ወቅት ነበር፡፡ በተወሰኑ ወጣት ምሁራን መሪነት በሚስጢር ተሰባስቦ ሲጽፍ፣ ሲወያይ፣ ጥናት ሲያካሂድ፣ ሲደራጅና ሲያደራጅ የቆየው እንቅስቃሴ ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ ያቋቋመበት፣ ትግሉ ከዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ አልፎ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተዛመተበት፣ ብሎም የብዙሃን ማኅበራትንም ሆነ የሕዝብን ድጋፍ እያገኘ የመጣበት ደረጃ ላይ ነበር፡፡ ስለዚህ የየካቲቱ 1966 አብዮት ግብታዊ ነበር የሚለው መከራከሪያ አጠቃላይ አብዮታዊ ሁኔታዎችን አስቀድሞ ማየት የተሳነው የሚመስለውም ለዚህ ነው፡፡

አርድ አንቀጥቅጥ የነበረው የየካቲት 66 አብዮት የተወለደው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት አልደፈርም በሚል ትኩረት የነሳቸው ቅርኔዎች ተከማችተው መፈንዳት በጀመሩበት ወቅት ነው። ወቅቱ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ሀገራዊ ጥያቄ የሆነበት፣ የንጉሡ አስተዳደር ፍፁም ከሕዝብ የተነጠለበት፣ የብዙኀኑ አስከፊ ድኽነትና የፍትህ እጦት ሕዝብን ያስመረረበት፤ ወገኖቻችን በረሃብ እያለቁ የጥቂት ባላባትና መኳንንት የቅንጦት ኑሮ ቅጥ ያጣበት፣ የሕዝብ ቁጣ ካፎቱ የወጣበትና የሥርዓት ለውጥ አይቀሬ ሆኖ የታየበት ጊዜ ነበር። ተማሪው፣ አስተማሪው፣ ገበሬው፣ ሠራተኛው፣ ወታደሩ፣ ታክሲ ነጅው፣ ...ወዘተ ቆርጦ ተነስቶ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት እንዲወገድና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ዘንድ ሕዝባዊ አብዮት ያካሄዱበት ታሪካዊ ወቅት ነው፡፡

ወቅቱ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው አብዮት የተካሄደበት ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ሕዝብ ታግሎ ያገኘውን ድል ባልጠበቀው ኃይል እየተጠነጠቀ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ በወቅቱ ትግሉ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አልፎ የትግሉ ማዕከል ሆኖ ሊመራ፣ ሊታገልና ሊያታግል የሚችል የመጀመሪያው ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ገና የተመሠረተ በመሆኑ፣ የተፈጠረውን የሥልጣን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ድርጅታዊ ጥንካሬ ገና አላገኘም ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ፓርቲው በወቅቱ ሁሉንም የሚያሳትፍ የሽግግር መንግሥት ለመመሥረት “የጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" የሚል ጥሪ በማስተጋባት፤ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ፣ ...ወዘተ በጽኑ ታግሏል። ሆኖም የነበረውን የሥልጣን ክፍተት በመጠቀም ወታደሩ “አብዮቱን በአድሀሪያን እንዳይቀለበስ ለመጠበቅ ” በሚል ሰበብ ሥልጣኑን ከሕዝብ ነጠቀ፡፡ ቀጥሎም ከ5 ዓመት በኋላ ወደ ወታደራዊ ሠፈራችን እንመለሳለን ሲል ዋሸ፤ ቀላመደ፡፡ ሃቁ ግን፣ እንኳንስ ሊመለስ 17 ዓመት ሙሉ በህዝብ ላይ ሽብር ከፍቶ፣ አንድ የተማረ ወጣት ትውልድ ጭዳ አድርጎ፣ ሀገራችንን ለፀረ-ኢትዮጵያ የብሔር ፅንፈኞች አመቻችቶላቸው ሄደ፡፡

ያ የተረበሸ ኮሎኔል በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ ወደ ሥልጣን መጥቶ ኢትዮጵያ ትቅደም በሚል ሽፍጥ የልጅ መካን አድርጓት አልፏል፡፡ ደርግ መሬት ለአራሹ እንዲሆን፣ ሥልጣን ከሕዝብ እንዲመነጭ ፀንቶ የታገለውን የ60-ዎቹን ወጣት ትውልድ

ቅርጥፍ አድርጎ በልቶ በፈጠረው ክፍተት፣ ወያኔ የተባለው የጠባብ ዘረኞች ቡድን ሥልጣን ተቆጣጥሮ፣ ለ27 ዓመት ሀገራችን እንዳታገግም አድርጎና አደባይቶ፤ በሃሰተኛ ትርክት ሀገርን አስገንጥሎ፤ ሕዝብን አለያይቶ፣ በሕዝብ ትግል ተገለለ። መገለል ብቻ ሳይሆን እብሪቱና ጉራው ዓይኑን ሸፍኖት ባደረገው ትንኮሳ አከርካሪቱን ተመታ። በቅርብ እንደታየው ወያኔ መቀሌ ላይ መሽጎ፣ ውጊያውን ብቻ ሳይሆን ጦርነትንም መሥራት እንችላለን እያለ በዕብሪት ሲደነፋ የከረመ ቢሆንም አንድ የነበረው ችሎታ ሰላማዊ ዜጎችን በውድቅት ሌሊት አድብቶ ማረድ እንደነበር አስመሰከረ፡፡ ለዚህ ነው ከሶስት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሱ በበቂ ያልታጠቁ የአማራ ልዩ ኃይል፣ ሚሊሻና ፋኖ በሩን በርግደው ገብተው ሲገጥሙት እግሬ አውጪኝ ብሎ፣ የቡድኑ ቁሳር ሳይቀር ከጉድጓዱ ጋማውን ተይዞ አደባባይ ላይ የወጣው፡፡ ገጣሚው

“አእምሮ ቢኖርህ የምታስብበት፣
ያን ጉድጓድ ባልቆፈርክ አንተው ልትገባበት”

ማለቱም ዕውን የሆነው፡፡

ቢሆንም የወያኔ ቁንጮዎች ተያዙ ወይም ሞቱ ብሎ አለቀ ደቀቀ ብሎ ከበሮ መደለቁና መዘናጋቱ የሚያዋጣ አይደለም፡፡ በተዛባ፣ የውሸትና መርዘኛ ትርክት ተወልደው ያደጉት በማይናቅ ብዛት አሁንም በየቦታው አሉና፡፡ ልክ ይኸው ዘረኛ ቡድን በአምሳሉ የቀረጻቸው በቁሮ መንጋ ሀገርንና ሕዝብን እያደባዩ እንዳሉት ማለት ነው፡፡

ከራሱ ከወያኔ ማህፀን የወጣውና ሁለተኛ ዙር የብሔር ፅንፈኝነትን ያስቀጠለው የኮሎኔሉ አገዛዝ የመቀሌው አውሬ ለሥልጣኑ መሰናከል እየሆነ ሲመጣና በአማራው ላይ ለተፈፀመው እልቂት ማዘናጊያም ይሁን በሌላ ምክንያት ተገፋፍቶ፣ ከኢትዮጵያ ጠላቶች አንዱ -ወያኔ- መመታቱ እሰዬው የሚያሰኝ ነው፡፡ ሆኖም ስብሃትን አስወግዶ በቦታው ከሻዕብያው ቁንጮ መመሪያ መቀበል፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ ዳግም ሀገር እንዲዘርፍና በሕዝብ ላይ የአፈና ወንጀል እንዲያሰፋ መጋበዙ፣ ለኮሎኔሉ ገሀድ የወጣ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

አማራው ደም ከፍሎ ያስመለሰውን መሬቱን ዳግም ለመንጠቅም ከብልጽግናዎቹ የሚደመጥ ሹክሹክታ ያለፈ እንደሚሆን ብዙ ሳይቆይ የሚጋለጥ ነው የሚሆነው፡፡ እስከ 80 የሚደርሱ ቋንቋዎች በሚነገሩባት አገር፣ አንድ ጎሳ በበላይነት እንዲገዛ ለማድረግ ከዕቅድ አልፎ ተቋም እየገነባ ሲሆን፣ በዛው ልክ ታሪኳንና ሕብረ ብሔራዊ እሴቶቿን ቀስ በቀስ በማፍረስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርግ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ፤ ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ፤ ለኢትዮጵያ አንድነት ሲባል፣ ... ነው ሕገመንግሥቱን የማንቀይረው በሚል የማይቀባጥረው፣ነገር የለም፡፡ የሚያሳዝነውና ከንቱ አሸቃባጭም ስለበዛ የልብ ልብ ተሰምቶት ሊሆን ይችላል፣ ይህ ዓይን ያወጣ ሸፍጡ ከመደጋገሙ የተነሳ የሕዝብ ጆሮም ማዳመጡን እያቆመ የመጣ ይመስላል፡፡

ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው አገራችን በተከታታይ አረመኔ አገዛዝ የተፈጥሮ ሀብቷን ብቻ ሳይሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የቁርጥ ቀን ልጆቿንም አሳጥቷታል፡፡ ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ትኩስ ኃይልና የአባቶቹን አደራ ተረካቢ ትውልድ መሆን እንዳለበት አይካድም፡፡ ይህ መርሕ ትግሉን ሲረከብና ሲቀጥል ኢሕአፓ በወጣት ኃይል በመገንባት ሲተገበር የቆዬው እውነታ ነው፡፡ እስከዛሬም በጊዜያዊ ጥቅም የደርግን፣ የወያኔንም ሆነ የኦፒዲኦን ፖለቲካ ሲያራምዱ አልተስተዋለም፡፡ በችግር የሚጠበሰውን ወገናቸውን ችላ ብለው ለሆዳቸው አላደሩም፡፡ በስለላ ሥራ ተሠማርተው ንፁሃንን ለጎጠኞችና ለዘረኞች አሳልፈው አልሰጡም፡፡ ምንም እንኳን ቀደም ሲል ኢሕአፓን ከድተው ወጥተው “ፎረም 84” በሚል ስያሜ

ለወያኔ የሰገዱ ጥቂት አንጃዎች እንደነበሩ ሁሉ፣ የአሁኖቹም ጭራሽ አይን አውጥተው፣ የድርጅቱን ስም ሰርቀው ሄደው ለኮሎኔሉ አገዛዝ የሰገዱ ጥቂት ከሀዲ አንጃዎች አልጠፉም፣ ኮሎኔሉም የባሰበት ግብዝ ነውና ሀራሬ ያለውን የደርግ ቁንጮ ከስደት ሊመልስ በሚመፃደቅበት አንደበቱ፣ ሰለባው የሆነውን ኢሕአፓ ለማጥቃት ግን ገና እንደተሾመ ነበር የጀመረው:: መስሎት ነው እንጅ እውነት በተረኝነት በሚያስቡ ደካሞች መንደር እንደማትኖር ሁሉ፣ ታሪክም ፀንተው በቆሙ ጀግኖች እንጅ ከደው በኮበለሉ ይሁዳዎች አይሠራም::

መሠረታዊና አንገብጋቢ የሆነው ጉዳይ፣ ሀገራችን ካለችበት ውጥንቅት ሁኔታ፣ መቅሰፍት ሆኖ ከተጋረጠባት የጠባብ ዘረኞች አገዛዝ፣ ካንዣበበባት የህልውና አደጋ ለመታደግ መፍትሄው የሚገኘው ችግርን ከፈጠረው ህሊና ወይም የአንድን ጎሳ የበላይነት በጎብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያ ላይ ለማስፈን፣ ከፊት ለፊት አስመሳይ የአንድነት፣ የኢትዮጵያዊነት ዲስኩር እያስደመጠ ሕዝብን በማጃጃል ከበስተጀርባ ለጠባብ ዓላማው መሠረት እየዘረጋ ካለው ኮሎኔል አይደለም:: መፍትሄው ያለው አሁንም ከሕዝቧ ብዛት ከ70% በላይ የሚሆነው ወጣት ኃይል ያለባት ሀገር ነችና ወጣቱ በስልት ተደራጅቶና የአንድነት ኃይሉን አቀናጅቶ በሚደያርገው ትግል ብቻ ነው መፍትሄ የሚሆነው:: ይህ ብቻ ነው ለሀገራችን መድህን የሚሆነው:: ዜጎች እንደዪዕምነታቸው፣ እንደዪርዕዮታቸው ለመኖር፣ የሚችሉት መጀመሪያ ያን ማድረግ የሚችሉበት ሀገር (ነፃነት) ሲኖር ብቻ በመሆኑ::

ስለዚህ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደዚያ ትውልድ፣ እስራት፣ ስየል፣ ግዞትና ሞት የማይበግራቸው ወጣት ጀግኖች ያስፈልጓታል:: ዛሬም አገራችን ካለችበት አጣብቂኝ ለመላቀቅ ሀገር ተረካቢና ለውጥ ፈላጊ፣ በጽናት የሚታገል፣ ለሐቅ የቆመ ወጣት ትውልድን ትሻለች:: ለፍትህና እኩልነት የሚታገል ትውልድን የምትናፍቅ ሀገር ነች:: ኢትዮጵያን መታደግ ዛሬም ታሪካዊ ኃለፊነትና ግዴታ በወጣቱ ትውልድ ላይ የተጣለ አደራ ነው:: ዛሬ ሀገራችን ዘረኝነትንና ኋላ ቀርነትን የሚጸየፍ፤ በተደራጀ ትግል ላይ እምነት ያለው ወጣት ትውልድ ትናፍቃለች። ወላድ በድባብ ትሂድ፣ ዛሬም ኢትዮጵያ በዓላማ ተደራጅተው፣ ለዓላማ የሚታገሉ፣ ውድ ሀገራቸውን የሚታደጉ ጀግኖች ወጣቶች አሏት። በመደራጀት ሀገር በዕኩልነትና በአንድነት እንድትቀጥል ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ዕውን መሆንም መታገላቸውን ይቀጥላሉ፤ ወደፊትም የበለጠ ታፈራለች በልጆቻም ታፍራና ተከብራ በልጽጋ እንድትኖር ያረጓታል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አገር አድን ትግል !